የኢትዮጵያ ልማት ባንክ መቐለ ዲስትሪክት የገነት ጠብታ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ለሰጠው ብድር አመላለስ በዋስትና የያዘውን የቲማቲም ማቀናበርያ ፋብሪካ ህንፃ ማሽነሪዎች እና ዕቃዎች እንዲሁም አይሱዙ ተሽከርካሪ ሞዴል NPR71H26 በአዋጅ ቁጥር 97/90 ፣ 216/92 እና 1147/11 በተሰጠው ስልጣን መሠረት በሐራጅ ለመሸጥ ይፈልጋል።

የተለቀቀበት ቀን: ረቡዕ ጉንበት 7, 2016 (ከ 1 ዓመት)
መዝግያ ቀን: ሓሙስ ሰነ 13, 2016 04:00 ጥዋት (ተዘጋ)
የጨረታ ማስከበርያ ዋጋ:25%
ቦታ:መቐለ
የጨረታ ደኩመንት ዋጋ:
ጨረታ ሚከፈትበት ቀንና ሰዓት: ሓሙስ ሰነ 13, 2016 04:10 ጥዋት
ምድብ: ገዛ/ህንፃ ምሻጥ/ ካልኦት ዝሸወጡ/

የሐራጅ ማስታወቂያ

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ መቐለ ዲስትሪክት የገነት ጠብታ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ለሰጠው ብድር አመላለስ በዋስትና የያዘውንና ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ የተመለከተውን ንብረት በአዋጅ ቁጥር 97/90፣ 216/92 እና 1147/11 በተሰጠው ስልጣን መሠረት በሐራጅ ለመሸጥ ይፈልጋል።

| የተበዳሪው መያዣ ሰጪው ስም | የመያዣ ንብረቱ አድራሻ | ለሐራጅ የቀረበ ንብረት ዓይነትና ዝርዝር | የቦታው ስፋት በካ/ሜ | የሐራጁ መነሻ ዋጋ / የሐራጁ ደረጃ በብር/ | ሐራጅ የሚካሄድበት ቀን እና ሰዓት |
|---|---|---|---|---|---|
| የገነት ጠብታ ኃ/የተ/የግ/ማህበር | በትግራይ ብ/ክ/ መንግስት ማዕከላዊ ዞን ዓድዋ ከተማ | የቲማቲም ማቀናበርያ ፋብሪካ ህንፃ ማሽነሪዎች እና ዕቃዎች እንዲሁም አይሱዙ ተሽከርካሪ ሞዴል NPR71H26 | 3500 ሜ/ካ | 10,538,627.77 አንደኛ /አስር ሚሊዮን አምስት መቶ ሰላሳ ስምንት ሺህ ስድስት መቶ ሀያ ሰባት ብር ከ77 ሣንቲም/ | ሰኔ 13 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 4:00-6:00 |

ማሳሰቢያ፡-

1. ተጫራቾች ንብረቱን ለመጎብኘት ከፈለጉ አሰቀድሞ ከባንኩ ጋር ቀጠሮ በመያዝ ከጨረታው ቀን በፊት ንብረቱን መጎብኘት ይችላሉ።

2. ተጨራቾች የጨረታውን መነሻ ዋጋ 25% (ሀያ አምስት በመቶ) በባንክ ማዘዣ ሲፒኦ (CPO) ብቻ አሰርተው ከጨረታው ቀን በፊት ማስያዝ ወይም ጨረታው በሚካሄድበት ዕለት ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል። በጨረታው የተሸነፉ ተጫራቾች ያስያዙት ሲፒኦ (CPO) ወዲያውኑ ይመለስላቸዋል።

3. በሐራጁ ለመሳተፍ የሚፈልግ ማንኛውም ተጫራች ጨረታው ከመጀመሩ በፊት ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት በፊት ባለው ጊዜ ጨረታው በሚካሄድበት ቦታ በአካል ወይም በህጋዊ ወኪል በኩል ቀርቦ መመዝገብ ይኖርበታል።

4. ጨረታው ከላይ በተገለፀው ቀንና ሰዓት ተበዳሪው/መያዣ ሰጪው ወይም ህጋዊ ወኪላቸው፣ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸውና ታዛቢዎች በተገኙበት በፕሮጀክቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ይካሄዳል። በጨረታ ቀንና ሰዓት መያዣ ሰጪው ወይም ህጋዊ ወኪላቸው እና ታዛቢዎች ባይገኙም ጨረታው ይካሄዳል።

5. በጨረታው የተሻለ ዋጋ ያቀረበ ተጫራች ማሸነፉን የሚገልፅ ደብዳቤ ከባንኩ ሲደርሰው አሸናፊ ይሆናል።

6. ጨረታውን ያሸነፈ ተጫራች አሸናፊ መሆኑ በፅሁፍ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ ያሸነፈበትን ዋና በ15 ተከታታይ ቀናት ጊዜ ውስጥ ለባንኩ አጠቃሎ ገቢ ማድረግ ይኖርበታል። በተገለፀው ጊዜ ውስጥ አሸናፊው ገንዘቡን ገቢ ካላደረገ ጨረታው ይሰረዛል፤ ያስያዘው ገንዘብም ለባንኩ ገቢ ይሆናል።

7. ጨረታው ያሸነፈ ተጫራች ያሸነፈበትን ገንዘብ በጥሬ ለባንኩ መከፈል ይኖረበታል።

8. የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለባቸው ተሽከርካሪ እና ማሽነሪዎች በተመለከተ ግዢው የቀረጥ ነፃ መብት ሊኖረው ይገባል ወይም በንብረቶቹ ላይ በመንግሰት የሚፈለገውን ቀረጥና ታክስ መክፈል ይኖርበታል። መን ወይም

9. የንብረቱ ስመ ንብረት ለገዢው እንዲዞር ባንኩ ለሚመለከተው መንግስታዊ አካል ደብዳቤ ይፅፋል። ገዢው ጉዳዩን ተከታትሎ ያስፈፅማል።

10. ጨረታው ከመካሄዱ በፊትም ሆነ ከተካሄደ በኋላ ባንኩ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ወይም ብድሩ ከተከፈለ ጨረታው የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

11. ጨረታው ያሸነፈ ተጫራች የሽያጩን 15% ተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሌሎች ገዥ እንዲከፍላቸው በሕግ የተወሰኑ ክፍያዎች፣ የስም ማዛወሪያ ክፍያን ጨምሮ ይከፍላል።

12. ለተጨማሪ መረጃ መቐለ ዲስትሪክት ሎን ዎርክአውት ዲቪዥን በአካል በመቅረብ ወይም በስልክ ቁጥር 034 440 7439: 034 441 9016 መግኘት ይችላሉ።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ መቐለ ዲስትሪክት